# የዋልድባ መቅሰፍት!!




ደረት ቢያሳብጡት !!

**በልዑል መጠግያ - በሱ ጥላ ያለ፣**

**በትሩን የጨበጠ - የወደቀ የታለ፣**

**መቼ ይሸነፋል - በሚበር ፍላጻ፣**

**ባጋዚዎች ጥይት - በትቢት አመጻ?**

በኅጢያት ተፅንሶ - ብርሃንን የማያይ፣

እርጉም የባንዳ ልጅ - ተወልደህ በምድርላይ፣

ስንቱን አስለቀስከው - እንባ አሳበስከው ፣

ኢትዮጵያን የጠላ - በሁከት የተበየ ፣

ገዳም የደፈረ - ካሕን ያሰቃየ ፣

ማስተውል ተስኖት - መለስ ብሎ ማየት፣

ሕዝቡን አስለቀሰ - ሽማግሌ አሮጊት ፣

ደረቱን ገልብጦ- ልክ እንደተራራ ፣

ደምሕን እጠጣለሁ - ብሎ የሚያስፈራራ፣

አኮ አሁን የታለ - ምነው አያጓራ ፣

የታል ያ ፉከራ - ምነው አያቅራራ?

ምነው አላዳነህ - ያሁሉ ወታደር ፣

የታል የፈውሰህ - የዶላሩ ክምር ?

**መስታወት ቢቀልጥ - ብረት ቢቀጠቀጥ፣**

**ጥይት እንዳይበሳው - ከምሮ ቢቀመጥ፣**

መች ከለላ ሆነህ - ምነው አላስጣለህ ?

የጎጥአንንም - ብድራት ይኸው ታየዋለህ፣

የሕዝቡንም ዕንባ - በፊትህ አኑረህ፣

ቁጣ በመውረዱ - መግቢያ መውጫ ጠፋ፣



ክቅጣት ኢያመልጥ - የሰው ሕይወት ያጠፉ።

ዘንዶውን እንዲረግጥ - ለሕዝቡ ቃል አለ፣

በመከራው ጊዜ እሱ - ከጎኑ አለ፣

እሱ የበቀል አምላክ - የሕዝብ ሁሉ ፈራጅ ፣

ለተጎዱ የሚደርስ - ይንጹሃን ወዳጅ።

በልዑል መጠግያ - በሱ ጥላ ያለ፣

በትሩን የጨበጠ - የወደቀ የታለ፣

መቼ ይሸነፋል - በሚበር ፍላጻ፣

ባጋዚዎች ጥይት - በትቢት አመጻ ።

ወዐማፅያንስ ይሴረዉ!!

(በደለኞች በአንድነት
ይጠፋሉ !! )



መይሳው ከምደረ ስዊድን 2012-08-08